**ትክክለኛ አይሁድ ለመሆን**

**ትክክለኛውን መሢህ ማወቅና**

**ቆራጥ  መሆን ያስፈልጋል**

ከሶስት መቶ (300 )በላይ በኦሪትና በብሉይ ኪዳን መፃህፍት በሚገኙ ጥቅሶች እንደተገለፀው  እውነተኛውና ትክክለኛው መሢህ እየሱስ  (የሹዋህ) ብቻ ነው!

ስለ መሢሁ ማንነት በኦሪትና በሌሎች የብሉይ ኪዳን መፃህፍት የተጠቀሱትን ሰባዎቹን (70) ዋና ዋና ጥቅሶችና በራሱ በንጉሡ  እየሱስ የተነገሩትን ጥቅሶች  በግል እንዲያጠኗቸው  ከዚህ በታች  ተዘርዝረዋል።

**ኢሳያስ 9:6-7**

6-<u>ህጻን ተወልዷልና ወንድ ልጅም</u> ተሰጥቷልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል
ዓምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።7- <u>ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለአለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ
ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና</u> በመንግስቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፤ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም።
የእግዚአብሄር ቅንዓት ይህን ያደርጋል።   (መሢሁ!)

**ሚክያስ 5:2,4**

2-አንቺም ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ አንቺ በይሁዳ አእላፋት ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ካንቺ ግን አወጣጡ
ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ <u>በእስራኤልም ላይ</u> <u>ገዢ</u> የሆነ ይወጣልኛል።4-እርሱም ይቆማል
በእግዚአብሄርም  ኃይል በአምላኩ በእግዚአብሄር ስም ግርማ መንጋውን ይጠብቃል እነርሱም ይኖራሉ እርሱ
እስከ ምድር ዳርቻ ታላቅ ይሆናልና።   (መሢሁ!)

**ዘፍጥረት 18:13-14**

13 እግዚአብሄርም  አብርሃምን አለው፦ካረጀሁብኋላ በውኑ እወልዳለሁን?ስትል ሣራ ለምን ሳቀች?በውኑ
ለእግዚአብሄር የሚሳነው ነገር አለን? ያዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ እመለሳለሁ፡ሣራም ልጅን
ታገኛለች።ሣራም ስለፈራች አልሳቅሁም ስትል ካደች።እርሱም፦አይደለም ሳቅሽ እንጅ አላት።

ኢሳያስ 7:14

ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ <u>ድንግል</u> ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል(እግዚአብሄር ከኛ ጋርነው ) ብላ ትጠራዋለች።(መሢሁ!)

ዘካሪያስ 12:10(በተጨማሪመዝሙር 22:7-22) (መሢሁ)

10- በዳዊትም ቤት ላይ በእየሩሳሌም ም በሚኖሩት ላይ የሞገስንና የልመናን መንፈስ አፈሳለሁ ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ።ሰውም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል፤ሰውም ለበኩር ልጁ እንደሚያዝን በመራራ ሃዘን ያዝኑለታል።

ዳንኤል7:9,13-14

ዙፋኖችም እስኪዘረጉ ድረስ አየሁ፤በዘመናት የሸመገለውም ተቀመጠ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ የራሱም ፀጉር እንዳ ጥሩ ጥጥ ነበረ……………….በሌሊት ራዕይ አየሁእነሆ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ ወደ ፊቱም አቀረቡት።ወገኖችና አህዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግስትም ተሰጠው ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው መንግስቱም የማይጠፋ ነው። (መሢሁ!)

ዘፍጥረት 49 :10 (በተጨማሪ ዘኍልቁ 24:17 ይመልከቱ) (መሢሁ!)

10-በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፤የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፤ገዢ የሆነው እስኪመጣ ድረስ <u>የአህዛብ መታዘዝም</u> ለእርሱ<u> ይሆናል።</u> ( በትረ መንግስት ከተለየ 2000 ዓመታት አለፉ ። በመሢሁ ዘመን ይሁዳን ሮማውያኖች ይገዙ እንደነበር ይታወቃል)።

ዳንኤል 9:26

26-ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሢህ ይገደላል፤በእርሱ ዘንድ ምንም የለም፦የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ(ሮማውያን ) ከተማይቱንና (እየሩሳሌምን) መቅደሱን ያጠፉሉ……………(ይህ ከሁለት ሺ ዓመት በፊት ተፈጽሟል።

**ዳንኤል** 3:24-25

**የዛን ጊዜም ንጉሡ ናቡከደናፆር ተደነቀ ፈጥኖም ተነሳ፤አማካሪዎቹንም ፡-ሶስት ሰዎች አስረን በእሳት ውስጥ ጥለን አልነበረምን? ብሎ ተናገራቸው።እነርሱም ንጉስ ሆይ እውነት ነው ብለው ለንጉሡ መለሱለት።እርሱም ፡- እነሆ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መካከል የሚመላለሱአራት ሰዎች አያለሁ፤ምንም አላቆሰላቸውም፤የአራተኛው መልክ <u>የአማልክትን ልጅ</u> ይመስላል ብሎ መለሰ። (መሢሁ!)**

**መዝሙር** 110:1(በንጉሥ ዳዊት የተፃፈ)

**እግዚአብሄር ጌታዬን** ፡-ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ **በቀኝ ተቀመጥ አለው። (መሢሁ)**

**ምሳሌ** 30:4

ወደ ሰማይ የወረደስ ማን ነው?ነፋስንስ በእጁ የጨበጠ ማን ነው? ውሃንስ በልብሱ የቋጠረ ማን ነው?የምድርን ዳርቻ ሁሉ ያጸና ማን ነው?ይህን ታውቅ እንደሆንህ <u>**ስሙ ማን የልጁስ ስም ማን ነው?**</u> **(መሢሁ**)

**ዘዳግም** 18:15-19 **(መሢሁ!**

አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደኔ ያለ **ነብይ**` (ሙሴ)ያስነሳልሃል **<u>እርሱንም ታዳምጣለህ</u>**።እግዚአብሔርም አለኝ፡-የተናገሩት መልካም ነው ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ **ነብይ** አስነሳላቸዋለሁ **ቃሌንም በአፉ** አደርጋለሁ፤ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል በስሜም **የምናገረውን ቃሌን የማይሰማውን** ሰው <u>**እኔ** እበቀልለታለሁ</u>።

**ኢሳያስ** 59:16–17,20 **[መሢሁ!]** (በተጨማሪኢሳያስ 635-6እንዲሁም **ሕዝቅኤል** 22:30 **ይመልከቱ**)

**ሰውም እንደሌለ** አየ ወደ እሱ **(ወደ ጌታ)የሚማልድ** እንደሌለ ተረዳ ተደነቀም ስለዚህ **የገዛ ክንዱ መድኀኒት አመጣለት ጽድቁም አገዘው።ጽድቅንም** እንደ ጥሩር ለበሰ፡በራሱም ላይ **የማዳንን** ራስ ቁር አደረገ፤የበቀልንም ልብስ ለበሰ፡በቅንዓትም መጐናጸፍያ ተጐናፀፈ።እንደስራቸው መጠን እንዲሁ ቁጣን ለባላጋራዎቹ ፍዳንም ለጠላቶቹ ይከፍላል። ለጽዮን **ታዳጊ** ይመጣል፡በያቆብም ዘንድ ከኃጢአት ለሚርቁይላል እግዚአብሔር።

**መዝሙር** 40:7-9 በዚያን ጊዜ አልሁ፡**እነሆ መጣሁ ስለኔ በመጽሐፍ ራስ ተጽፏል**።አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድኩ **ሕግህ በልቤ ውስጥ ነው** ።እነሆ ከንፈሮቸን አልከለክልም።አቤቱ **አንተ ጽድቄን ታውቃለህ**። **[መሢሁ!]**

**ኢሳያስ** 52፡10,13-15 **እግዚአብሔር** **<u>የተቀደሰውን ክንዱን</u>** በአህዛብ ሁሉ ፊት ገልጧል።**በምድር ዳርቻ የሚኖሩትም ሁሉ የአምላካችንን መድኃኒት ያያሉ**።

እነሆ **<u>ባሪያዬ</u>** በማስተዋል ያደርጋል **ይከብራል ከፍ ከፍም ይላል እጅግ ታላቅም ይሆናል**።**ፊቱ ከሰዎች ሁሉ ይልቅ መልኩም ከሰዎች ልጆች ይልቅ ተጐሳቁሏልና** ብዙ ሰዎች ስለ አንተ <u>ተደነቁ፡እንዲሁ ብዙ አህዛብን ያስደንቃል(**በደሙ**) ፡ያልተነገረላቸውንም ያያሉና ያልሰሙትንም ያስተውላሉና ነገሥታት ስለ እርሱ አፋቸውን ይዘጋሉ</u>። **[መሢሁ]**

**ኢሳያስ** 53፡1 ,4-6,11 የሰማነውን ነገር ማን አምኗል **<u>የእግዚአብሔርስ ክንድ</u>** ለማን ተገልጧል? **[መሢሁ!]**

በእውነት **ደዌያችንን ተቀበለ** ሕመማችንንም ተሸክሟል እኛ ግን **እንደ ተመታ** በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሰፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው ።**እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ ስለ በደላችንም ደቀቀ** የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ **<u>ነበረ፡በእርሱም ቁስል (በደሙ)እኛ ተፈወስን(ዳን)</u>**<u>።እኛ</u> ሁላችን እንደ በጐች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል **ኃጢያታቸውንም ይሸከማል**።

**መዝሙር** 22፡1 16 **አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ**?

**እጆቼንና እግሮቸን ቸነከሩኝ(ደሙ) [መሢሁ]**

**ዘካርያስ** 9፡9-11

አንቺ የጺዮን ልጅ ሆይ እጅግ ደስ ይበልሽ አንቺ የእየሩሳሌም **ልጅ** ሆይ እልል በይ እነሆ **ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው ትሁትም ሆኖ** በአህያም በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል።**ለአህዛብም ሰላምን ይናገራል** ግዛቱም ከባህር እስከ ባህር ከወንዝም እስከምድር ዳርቻ ድረስ ይሆናል።ለአንቺም ደግሞ **<u>ስለ ቃልኪዳንሽ ደም(የመሢሁ</u>**) እስሮችሽን ውሃ ከሌለበት ጉድጓድ አውጥቻለሁ። **[መሢሁ!]**

**ኤርምያስ 31:31-34**

እነሆ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ (ደሙ)ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ይላል እግዚአብሔር ።ከግብጽ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝኩበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋርእንደገባሁት ያለ ቃልኪዳን አይደለም እነሱ በኪዳኔ አልጸኑምና እኔም ቸል አልኋቸውይላል እግዚአብሔር።ከእነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃልኪዳን ይህ ነውና ይላል እግዚአብሔር ፤ ሕጌን በልቦናቸው አኖራለሁ በልባቸውም እጽፈዋለሁ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል።እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን እያንዳንዱም ወንድሙን እግዚአብሔርን እወቅ ብሎ አያስተምርም፤ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና ይላል እግዚአብሔር ።በደላቸውን እምራቸዋለሁ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና።(በደሙ በገባው ዘላለማዊ ቃልኪዳን)

**ዘፍጥረት 3:15 [መሢሁ!]**

“በአንተና(ሰይጣን) በሴቲቱ (ሔዋን)መካከል በዘርህና በዘርዋም (ከዘርዋ የሚገኘው መሢሁ)መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ እራስህን(ሰይጣን) ይቀጠቅጣል አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ(ደሙ)”

**ዘለዋውያን 17:11**

የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና ደሙም ከሕይወቱ የተነሳ ያስተሰረያልና በመሰዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተሰርያ ይሆን ዘንድ እኔ ለናንተ ሰጠሁት።

**ሕዝቅኤል 36:25-28**( በተጨማሪ ሕዝቅኤል 11:19-20 16:60 18:31-32 ይመልከቱ)።

ጥሩ ውሃንም እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ፤ከርኩሰታችሁም ሁሉ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ።አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ።መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ።በትዕዛዜም አስኬዳችኋለሁ፤ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ ።ለአባቶቻችሁም በሰጠኋት ምድር ትኖራላችሁሕዝብም ትሆኑኛላችሁእኔም ዓምላክ እሆናችኋለሁ።

**መዝሙር 118፡22-26**

ግንበኞች የናቁት **ድንጋይ** እርሱ **<u>የማዕዘን ራስ</u>** ሆነ፤ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች ለዐይናችንም ድንቅ ናት። እግዚአብሔር የሰራት ቀን ይህች ናት ሐሴትን እናድርግ በርሷም ደስ ይበለን።አቤቱእባክህ አሁን አድን፤ አቤቱእባክህ አሁን አቅና፤ **በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ** ብሩክ **ነው** ከእግዚአብሔር ቤት መረቅናችሁ። **[መሢሁ]**

**ኢሳያስ 63፡8-10**

እርሱም በእውነት ሕዝቤ ሐሰትን የማያደርጉ ልጆች ናቸው አለ **መድኃኒትም ሆነላቸው**። **<u>በጭንቃቸውም ሁሉ እርሱ ተጨነቀ የፊቱም መልዓክ</u> አዳናቸው** በርኅራኄውም ተቤዣቸው።በቀደመውም ዘመን ሁሉ አንስቶ ተሸከማቸው።እነሱ ግን አመጹ **ቅዱስ መንፈሱንም** አስመረሩ ስለዚህ ተመልሶ ጠላት ሆናቸው እርሱም ተዋጋቸው። **[መሢሁ!]**

**ኢሳያስ 42፡1-4,6-7 [መሢሁ!]**

እነሆ ደግፌ የያዝሁት **ባሪያዬ** ነፍሴ **ደስ** የተሰኘችበት **ምርጤ በእርሱ ላይ መንፈሴን** አድርጌያለሁ፤እርሱም ለአሕዛብ ፍርድን ያወጣል።አይጮህም ቃሉንም አያነሳም ድምጹንም በሜዳ አያሰማም።የተቀጠቀጠን ሸንበቆ አይሰብርም፤የሚጤስንም ክር አያጠፋም በእውነት ፍርድን ያወጣል።በምድርም **ፍርድን** እስኪያደርግ ይበራል እንጂ አይጠፋም አሕዛብም በስሙ ይታመናሉ።እኔ እግዚአብሔር በጽድቅ ጠርቼሃለሁ፤እጅህንም እይዛለሁ እጠብቅሃማለሁ፤የዕውሩንም ዓይን ትከፍት ዘንድ የተጋዘውንም ከግዞት ቤት በጨለማም የተቀመጡትን ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ **<u>ለሕዝብ ቃል ኪዳን ለአሕዛብም ብርሃን አድርጌ እሰጥሃለሁ።</u>**

**መዝሙር 82፡6**

እኔ ግን ፦ "አማልክት ናችሁ፡ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ።"

**ዘካርያስ 13፡7-9  [መሢሁ]**

ሰይፍ ሆይ ባልንጀራዬ በሆነው ሰው በእረኛዬ ላይ ንቃ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤እረኛውን ምታ በጐቹም ይበተናሉእጄንም በታናናሾች ላይ እመልሳለሁ።በምድርም ሁሉ ላይ ሁለት  ክፍል ተቆርጠውይሞታሉ፤ ይላል እግዚአብሄር፥ሶስተኛውም ክፍል ከእርሷ ውስጥ ይቀራል።ሶስተኛውንም ክፍል ወደ እሳት አገባለሁ፡ብርም እንደሚነጥር አነጥራቸዋለሁ።ወርቅም እንደሚፈተን እፈትናቸዋለሁ።እነርሱም ስሜን ይጠራሉእኔም እሰማቸዋለሁ፤እኔም ይህ ሕዝቤ ነው እላለሁ፤እርሱም እግዚአብሔር አምላኬ ነው ይላል።

**ኢሳያስ 49:5-9** (በተጨማሪ 10 ይመልከቱ)

አሁንም  በእግዚአብሔር ዓይን ከብሬአለሁና አምላኬም ጉልበት ሆኖኛልና ያዕቆብን ወደ እርሱ እንድመልስ እስራኤልንም ወደ እርሱ እንድሰበስብ ባሪያ እሆነው ዘንድ ከማህፀን ጀምሮ የሰራኝ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።እርሱም የያዕቆብን ነገዶች እንድታስነሳ ከእስራኤልም የዳኑትን እንድትመልስ ባሪያዬ ትሆን ዘንድ እጅግ ቀላል ነገር ነውና  እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ መድኃኒት ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን  አድርጌ ሰጥቼሃለሁ ይላል። የእስራኤል ታዳጊ ቅዱስም እግዚአብሔር ሰዎች ለሚንቁት ሕዝብም ለሚጠላው ለገዥዎች ባሪያ እንዲህ ይላል፥ ስለ ታማኙ ስለ እግዚአብሔር ስለ መረጠህም ስለ እስራኤል ቅዱስ ነገሥታት አይተው ይነሳሉ መሳፍንትም አይተው ይሰግዳሉ።እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል፥በተወደደ ጊዜ ሰምቼሃለሁ በመድኃኒትም ቀን እረድቼሃለሁ እጠብቅህማለሁ ምድርንም ታቃና ዘንድ ውድማ የሆኑትንም ርስቶች ታወርስ ዘንድ የተጋዙትንም ውጡ በጨለማም የተቀመጡትን ተገለጡ ትል ዘንድ ቃል ኪዳን አድርጌ ለሕዝቡ ሰጥቼሃለሁ።በመንገድም ላይ ይሰማራሉ ማሰማሪያቸውም በወና ኮረብታ ሁሉ ላይ ይሆናል።  [መሢሁ!]

**ዘካሪያስ 3፡6, 8-9**(በተጨማሪ 1-4 ያሉትን ጥቅሶች ያንብቡ)

የእግዚአብሔር መልአክ በኢያሱ እንዲህ ሲል አዳኘበት፥ታላቁ ካህን ኢያሱ ሆይ(ከአሮን ወገንከሆነው የጳዶቅ ቤተሰብ)፤ስማ በፊትህም የሚቀመጡት ባልንጀሮችህ ለምልክት የሚሆኑ ሰዎች ናቸውና ይስሙ እነሆ ባሪያዬን ቁጥቋጥ (መሢሁ) አወጣለሁ።በኢያሱ ፊት ያኖርኩት ድንጋይ እነሆ አለ በአንዱ ድንጋይ ላይ ሰባት ዓይኖች አሉ እነሆ ቅርጹን እቀርጻለሁ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤የዚያችን ምድር በደል በአንድ ቀን አስወግዳለሁ [መሢሁ]።

**ዘፍጥረት 14፡18-20 [መሢሁ]**

**የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም እንጀራና የወይን ጠጅንም አወጣ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር።**
ባረከውም ፥አብራም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው፡ጠላቶችህን በእጅህ
የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔርም የተባረከ ነው አለውም። አብራም ም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው (ለመልከ
ጼዴቅ)።

**ዘካርያስ 6:11-13**(እዝራ 3፡2 )

ብርንና ወርቅን ከነሱ ውሰድ **አክሊሎችንም** ሥራ በታላቁም **ካህን** በኢዮሴዴቅ ልጅ በኢያሱ ላይ ድፋቸው።
እንዲህም በለው፥ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥**እነሆ ስሙ ቁጥቋጥ** የሚባል ሰው በሥፍራው
**ይበቅላል፤የእግዚአብሔርንም መቅደስ** ይሠራል።እርሱ የእግዚአብሔርን መቅደስ ይሠራል።ክብርንም ይሸከማል፡
በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ **ይነግሣል**፤በዙፋኑም ላይ ካህን ይሆናል፤የሰላም ም ምክር **በሁለቱ መካከል** ይሆናል።"
**(ንጉሥና ካህን) [መሢሁ!]**

**ዘፍጥረት 22፡8, 10-18**(በተጨማሪዘፍጥረት 18፡1-2, 10, 16-18, 22 ይመልከቱ)

አብርሃም ም **ልጄ ሆይ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል** አለው፤ሁለቱም አብረው ሄዱ።አብርሃም ም
እጁን ዘረጋ ልጁንም ያርድ ዘንድ ቢላዋ አነሳ።የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ ጠራና፥አብርሃም አብርሃም
አለው እርሱም እነሆኝ አለ።እርሱም ፥ብብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ አንዳችም አታድርግበት አንድ ልጅህን
ለኔ አልከለከልክምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደሆንክ አሁን አውቄያለሁ አለ። አብርሃም ም ዓይኑን አነሳ
በኋላውም **አንድ በግ** በዱር ውስጥ **ቀንዶቹ** በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤አብርሃም ም ሄደ በጉንም ወሰደው በልጁም
ፋንታ መሥዋዕት አድርጐ ሠዋው።አብርሃም ም ያንን ቦታ **ያህዌ ይርኤ** ብሎ ጠራው ።እስከ ዛሬም ድረስ
በእግዚአብሔር ተራራ ይታያል ይባላል። **የእግዚአብሔር መልአክም** አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው፤
እንዲህም አለው ፥እግዚአብሔር ፥ "**በራሴ ማልሁ ይላል** ይህን ነገር አድርገሃልና **አንድ ልጅህንም**
አልከለከልህምና በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፡ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ
አበዛዋለሁ ፤**ዘርህም (መሢሁ)**የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል፤የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ፤ቃሌን
ሰምተሃልና።"

*መዝሙር* 2:6-7 ,12 **እኔ ግን "ንጉሤን" ሾምሁ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ።**

ትዕዛዙን እናገራለሁ ፡-እግዚአብሔር አለኝ፡-**አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ**።ተግሣጹን ተቀበሉ ጌታ እንዳይቆጣ እናንተም በመንገድ እንዳትጠፉ፤ቁጣው ፈጥና ትነዳለችና።**በእርሱ** (**መሚሁ**) የታመኑ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው።

**ዘፍጥረት 32:24 ,28, 30** (በተጨማሪ ሆሴዕ 13:4 ይመልከቱ -----**ከመልአኩ** ጋር ታገለ---)

ያዕቆብ ግን ለብቻው ቀረ፡አንድ **ሰውም** እስከ ንጋት ድረስ ይታገለው ነበር። ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጅ ያዕቆብ አይባል **ከእግዚአብሔር** ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና።ያዕቆብም **እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ** ሰውነቴም ድና ቀረች ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል ብሎ ጠራው። [**መሚሁ**]

**ዘፀአት 3:2-6 [መሚሁ]**

**የእግዚአብሔርም መልአክ** በእሳተ ነበልባል በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል ታየው፡እነሆም ቁጥቋጦው በሳት ሲነድ ቁጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ።ልሂድና ቁጥቋጦው ስለ ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራዕይ ልይ አለ። እግዚአብሔር እርሱ፡ይመለከት ዘንድ እንደመጣ ባየ ጊዜ **እግዚአብሔር እርሱን ጠርቶ** ፡-ሙሴ ሙሴ ሆይ አለ። እርሱም እነሆኝ አለ።ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምክባት ሥፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው።ደግሞም ፡-**እኔ የአባትህ አምላክ** የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ ነኝ አለው።

**ዘፀአት 23:20-23 [መሚሁ]**

በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ሥፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆ እኔ **መልአክን** በፊትህ እሰዳለሁ።በፊቱ **ተጠንቀቁ ቃሉንም አድምጡ ስሜም በሱ ስለሆነ** ኃጢአት ብትሰሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት።አንተ ግን **ቃሉን ብትሰማ** ያልኩህንም ሁሉ ብታደርግ ጠላቶችህን እጥላቸዋለሁ ፤የሚያስጨንቁህን ሁሉ አስጨንቃቸዋለሁ። **መልአኬ** በፊትህ ይሄዳልና ወደ አሞራውያንም ወደ ኬጢያውያንም ወደ ፌርዝያውያንም ወደ ኤውያውያንም ወደ ኢያቡሣውያንም ያገባሃል እኔም አጠፋቸዋለሁ።

**መሳፍንት 13: 3 ,18, 20, 22 [መሚሁ!]**

**የእግዚአብሔርም መልአክ** ለሴቲቱ ተገልጦ እንዲህ አላት፡-"እነሆ አንቺመካን ነሽ ልጅም አልወለድሽም ነገር ግን ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ።"

**ኢያሱ 5፡13-15 [መሲሁ!]**

እንዲህም ሆነ ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ ዓይኑን አንስቶ ተመለከተ፤እነሆም የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ **ሰው** በፊቱ ቆሞ ነበር፤ኢያሱም ወደ እርሱ ቀርቦ ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን አለው።እርሱም **አይደለሁም እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆ፞ኜ** አሁን መጥቻለሁ አለ።ኢያሱም በግምባሩ ተደፍቶ **ሰገደና**፥ **ጌታዬ** ለባሪያው የሚነግረው ምንድን ነው?አለው።**የእግዚአብሔርም የሠራዊት አለቃ** ኢያሱን፥አንተ የቆምክበት ሥፍራ **የተቀደሰ** ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው።ኢያሱም እንዲሁ አደረገ።

**የእግዚአብሔርም መልአክ**፥ስሜ **ድንቅ** ነውና ለምን ትጠይቃለህ አለው።ነበልባሉም ከመሰዊያው ላይ ወደ ሰማይ በወጣ ጊዜ **የእግዚአብሔር መልአክ** በመሰዊያው ነበልባል ውስጥ ዐረገ ማኑሄና ሚስቱም ተመለከቱ፤ በምድርም በግምባራቸው ተደፉ።ማኑሄም ሚስቱን **እግዚአብሔርን አይተናልና** እንሞታለን አላት።(ኢሳያስ 9፡6 ይመልከቱ)"የዚህን ህግ ቃሎች ያደርግ ዘንድ የማያጸና ርጉም ይ ሁን ሕዝቡም ሁሉ **አሜን** አሉ።"(**ዘዳግም 27:26)**

**ኤርምያስ 23: 5-6**

እነሆ፥ ለዳዊት **ጻድቅ ቍጥቋጥ**(ልጅ) የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር፥ እርሱም እንደ **ንጉሥ ይነግሣል**፥ ይከናወንለታልም፥ በምድርም ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል። በዘመኑም ይሁዳ ይድናል እስራኤልም ተዘልሎ ይቀመጣል፥ **የሚጠራበትም ስም እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው።**

**ኤርምያስ፡14-18 [መሲሁ]**

እነሆ፥ ስለ እስራኤል ቤትና ስለ ይሁዳ ቤት የተናገርሁትን መልካም ቃል የምፈጽምበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር። በዚያም ዘመን በዚያም ጊዜ ለዳዊት **የጽድቅን ቍጥቋጥ** አበቅልለታለሁ፤ **እርሱም** ፍርድንና ጽድቅን በምድር ያደርጋል። በዚያም ዘመን ይሁዳ ይድናል ኢየሩሳሌምም ተዘልላ ትቀመጣለች፤ የምትጠራበትም ስም። **"እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው።"**
እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። በእስራኤል ቤት ዙፋን ላይ የሚቀመጥ **ሰው** ከዳዊት ዘንድ አይታጣም፤ የሚቃጠለውንም መሥዋዕት የሚያቀርብ የእህሉንም ቍርባን የሚያቃጥል **ሁልጊዜም የሚሠዋ ሰው ከሌዋውያን ካህናት ዘንድ በእኔ ፊት አይታጣም።[ከዳዊትና ከሊቀ ካህኑከጻዶቅ ዘር የሆነው ካህንና ንጉሥ የሆነው መሲሁ]**

**ዘካሪያስ 9:14-16**(በተጨማሪ ኢሳያስ 27: 13ይመልከቱ) **[መሢሁ]**

**እግዚአብሔርም** በእነርሱ ላይ ይገለጣል፥ ፍላጻውም እንደ መብረቅ ይወጣል፤ **<u>ጌታ እግዚአብሔርም መለከትን ይነፋል፥</u>** በደቡብም ዐውሎ ነፋስ ይሄዳል።
**የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይጠብቃቸዋል፤** እነርሱም ይበሉአቸዋል፥ የወንጭፉንም ድንጋዮች ይረግጣሉ፤ እንደ ወይን ጠጅም ይጠጡአቸዋል፥ እንደ ጥዋዎችም እንደ መሠዊያም ማዕዘኖች የተሞሉ ይሆናሉ።
**በዚያም ቀን አምላካቸው እግዚአብሔር** እንደ ሕዝቡ መንጋ ያድናቸዋል፤ እነርሱም ለአክሊል እንደሚሆኑ እንደ ከበሩ ድንጋዮች ይሆናሉ፥ በምድሩም ላይ ይብለጨለጫሉ።

**መዝሙር 24:7-10 [መሢሁ]**

እናንት መኳንንቶች፥ በሮችን ክፈቱ፥ የዘላለም ደጆችም ይከፈቱ፥ **የክብርም ንጉሥ ይግባ።**
ይህ **የክብር ንጉሥ ማን ነው?** እግዚአብሔር ነው፥ ብርቱና ኃያል፥ እግዚአብሔር ነው፥ በሰልፍ ኃያል።
እናንተ መኳንንቶች፥ በሮችን ክፈቱ፥ የዘላለም ደጆችም ይከፈቱ፥ የክብርም ንጉሥ ይግባ።
**ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው? <u>የጭፍሮች አምላክ እግዚአብሔር፥</u> እርሱ የክብር ንጉሥ ነው።** ሴላህ

**ኢሳያስ 16:5**

**ዙፋንም** በምሕረት ይቀናል፥ በዚያም ላይ **በዳዊት ድንኳን ፍርድን** የሚሻ **ጽድቅንም** የሚያፈጥን **ፈራጅ በእውነት** ይቀመጣል።**[መሢሁ]።**

**ዳንኤል 10 :5-6 ,14 ,21**

እነሆም፥ በፍታ የለበሰውን ጥሩም የአፌዝን ወርቅ በወገቡ ላይ የታጠቀውን **ሰው** አየሁ።
አካሉም እንደ ቢረሌ ይመስል ነበር፥ **ፊቱም እንደ መብረቅ ምስያ** ነበረ፥ **ዓይኖቹም እንደሚንበለበል** ፋና፥ ክንዶቹና እግሮቹም እንደ ጋለ ናስ፥ **የቃሉም ድምፅ** እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ነበረ። ራእዩም ገና ለብዙ ዘመን ነውና በኋለኛው ዘመን ለሕዝብህ የሚሆነውን አስታውቅህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ።ነገር ግን **በእውነት ጽሑፍ** የተጻፈውን እነግርሃለሁ፤ በዚህም ነገር ከአለቃችሁ ከሚካኤል በቀር ማንም የሚያጸናኝ የለም።**[መሢሁ]**

**ዳንኤል 12:6-7**

**አንዱም** ከወንዙ ውኃ በላይ የነበረውን በፍታም የለበሰውን። የዚህ ድንቅ ፍጻሜ እስከ መቼ ነው? አለው።

7 **ከወንዙም ውኃ በላይ የነበረው በፍታም የለበሰው ሰው ቀኙና ግራ እጁን ወደ ሰማይ አንሥቶ። ለዘመንና ለዘመናት ለዘመንም እኵሌታ ነው፤ የተቀደሰውም ሕዝብ ኃይል መበተን በተጨረሰ ጊዜ ይህ ሁሉ ይፈጸማል ብሎ ለዘላለም ሕያው ሆኖ በሚኖረው ሲምል ሰማሁ።** (ዘዳግም 32:39-40 **ይመልከቱ**) **[መሢሁ]**

**ኢሳያስ 11:1-2 ,4-5** (በተጨማሪ ኢሳያስ 61: 1-3 **ይመልከቱ**) **[መሢሁ]**

ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፥ ከሥሩም **ቍጥቋጥ** ያፈራል።

**የእግዚአብሔር መንፈስ፥ የጥበብና የማስተዋል** መንፈስ፥ የምክርና የኃይል መንፈስ፥ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ **ያርፍበታል።**

ነገር ግን ለድሆች በጽድቅ ይፈርዳል፥ ለምድርም የዋሆች በቅንነት ይበይናል፤ በአፉም በትር ምድርን ይመታል፥ በከንፈሩም እስትንፋስ **ክፉዎችን ይገድላል።**

የወገቡ መታጠቂያ ጽድቅ፥ የጎኑም መቀነት **ታማኝነት** ይሆናል።

**መዝሙር 89:20-21 ,26-29 ,35-36** (በተጨማ 3, 4, 34, 37 **ይመልከቱ**) **[መሢሁ]**

**ባሪያዬን ዳዊትን** አገኘሁት፥ ቅዱስ ዘይትም ቀባሁት።

እጄም ትረዳዋለች፥ ክንዴም ታጸናዋለች።

እርሱ **አባቴ አንተ ነህ፥ አምላኬ የመድኃኒቴም መጠጊያ** ይላል።

እኔም ደግሞ **በኵሬ አደርገዋለሁ፥ ከምድር ነገሥታትም ከፍ ይላል።**

ለዘላለምም ምሕረቴን ለእርሱ እጠብቃለሁ፥ ኪዳኔም በእርሱ ዘንድ የታመነ ነው።

**ዘሩንም (መሢሁ)**ለዓለምና **ለዘላለም፥ ዙፋኑንም** እንደ ሰማይ ዘመን አደርጋለሁ።

ዳዊትን እንዳልዋሸው አንድ ጊዜ በቅዱስነቴ ማልሁ።

**ዘሩ ለዘላለም፥ ዙፋኑም** በፊቴ እንደ ፀሐይ ይኖራል-----

**1ኛ ዜና መዋዕል 17:10-15** (በተጨማሪ 2ኛ ሳሙኤል7:5 12-16 **ይምልከቱ**)

እግዚአብሔር ደግሞ ቤት እንዲሠራልህ እነግርሃለሁ።

ወደ አባቶችህም ትሄድ ዘንድ ዕድሜህ በተፈጸመ ጊዜ ከልጆችህ የሚሆነውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ፤ **መንግሥቱንም አጸናለሁ።**

**እርሱ ቤት ይሠራልኛል፤ ዙፋኑንም ለዘላለም አጸናለሁ።**

**እኔም አባት እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል፤** ከአንተ አስቀድሞ ከነበረው እንዳራቅሁ፥ ምሕረቴን ከእርሱ አላርቅም።
**በቤቴና በመንግሥቴም** ለዘላለም አቆመዋለሁ፤ ዙፋኑም ለዘላለም ይጸናል።
እንደዚህ ነገር ሁሉ እንደዚህም ራእይ ሁሉ ናታን ለዳዊት ነገረው። **[መሢሁ]**

**ኢሳያስ 53:1–12**

የሰማነውን ነገር **ማን አምኖአል? የእግዚአብሔርስ ክንድ** ለማን ተገልጦአል?
በፊቱ እንደ ቡቃያ ከደረቅም መሬት እንደ ሥር አድጎአል። መልክና ውበት የለውም፥ ባየነውም ጊዜ እንወድደው ዘንድ ደም ግባት የለውም።
የተናቀ ከሰውም የተጠላ፥ **የሕማም ሰው ደዌንም** የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፥ እኛም አላከበርነውም።
<u>በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል</u>፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው።
እርሱ ግን ስለ **መተላለፋችን ቈሰለ፥** ስለ **በደላችንም ደቀቀ፤** የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ **<u>በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።</u>**
እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ **እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።**
**ተጨነቀ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም።**
በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ **ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ** ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ?
ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፥ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፥ በአፉም ተንኰል አልተገንበትም ነበር።
እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፤ **<u>ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ</u>** በኋላ ዘሩን ያያል፥ ዕድሜውም ይረዝማል፥ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል።
**ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል፤ ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥** ኃጢአታቸውን ይሰከማል።
ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፥ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ **ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፥** ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና፤ እርሱ ግን **የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፥** ስለ ዓመፀኞችም ማለደ።

**ኢሳያስ 61:1-2**

**የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥** ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፤ **ልባቸው** የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፥ ለተማረኩትም ነጻነትን ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ **ልኮኛል።**
**የተወደደችውን** የእግዚአብሔርን **ዓመት** አምላካችንም **የሚበቀልበትን ቀን** እናገር ዘንድ፥ የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ፤

**ዳንኤል 2:34-35**

እጅም ሳይነካው **ድንጋይ** ከተራራው ተፈንቅሎ ከብረትና ከሸክላ የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታና ሲፈጭ አየህ።**[መሢሁ !]**
የዚያን ጊዜም ብረቱና ሸክላው፥ ናሱና ብሩ ወርቁም በአንድነት ተፈጨ፥ በመከርም ጊዜ በአውድማ ላይ እንዳለ እብቅ ሆነ፤ ነፋስም ወሰደው፥ ቦታውም አልታወቀም፤ ምስሉንም የመታ ድንጋይ ታላቅ **ተራራ ሆነ ምድርንም ፈጽሞ ሞላ።**

**ኢሳያስ 28:16** (መዝሙር 118:22 የማዕዘኑ ድንጋይ)

ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። እነሆ፥ በጽዮን **ድንጋይን** ለመሠረት አስቀምጣለሁ፤ የተፈተነውን፥ የከበረውን፥ መሠረቱ የጸናውን **የማዕዘን ድንጋይ(መሢሁ)**የሚያምን አያፍርም።**[መሢሁ!**

**ኢሳያስ 8:14-15**

እርሱም **ለመቅደስ** ይሆናል፤ ነገር ግን ለሁለቱ ለእስራኤል ቤቶች **ለዕንቅፋት ድንጋይና ለማሰናከያ ዓለት፥** በኢየሩሳሌም ም ለሚኖሩ ለወጥመድና ለአሽክላ ይሆናል።
ብዙዎችም በእርሱ ይሰናከላሉ፥ ይወድቁማል፥ ይሰበሩማል፥ ይጠመዱማል፥ ይያዙማል። **[መሢሁ!]**
**ዘፍጥረት1:26, ዘፍጥረት 3:22 , ዘፍጥረት 11:7 , ኢሳያስ 6:8 , ኢሳያስ 48:16**
**እግዚአብሔርም አለ ሰውን <u>በመልካችን</u> እንደ <u>ምሳሌአችን</u> እንፍጠር፤** የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ **በምድር** ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ **ይግዙ።**እግዚአብሔር አምላክም አለ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ **ከእኛ እንደ አንዱ** ሆነ፤ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፥ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፥ ለዘላለምም ም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር ።ኑ **እንውረድ** አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ **እንደባልቀው።** የጌታንም ድምፅ **ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል?** ሲል ሰማሁ። እኔም እነሆኝ እኔን ላከኝ አልሁ።ወደ እኔ ቅረቡ ይህንም ስሙ፤ እኔ ከጥንት ጀምሬ በስውር አልተናገርሁም፤ ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበርሁ፥ **አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል።**

**መዝሙር 8:4-6**

*ታስበው ዘንድ ሰው **ምንድር** ነው? ትጐበኘውም ዘንድ **የሰው ልጅ ምንድር** ነው?*
***ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው፤** በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው።*
***በእጆችህም** ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው **ሁሉን** ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት።*
***መዝሙር**14:3ሁሉ ዐመፁ **በአንድነትም ረከሱ** በጎ ነገርን የሚሠራ የለም፤ አንድም ስንኳ የለም።(በተጨማሪ መዝሙር*
53:1, 3 ይመልከቱ)

**ሆሴዕ 2:1**

የእስራኤልም ልጆች ቍጥር እንደማይሰፈርና እንደማይቈጠር እንደ ባሕር አሸዋ ይሆናል፤ እንዲህም ይሆናል፤ እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም ተብሎ በተነገረበት በዚያ ስፍራ **የሕያው አምላክ ልጆች ይባላሉ።**

**ኢሳያስ 59:1-2**

***እነሆ የእግዚአብሔር እጅ** ከማዳን አላጠረችም፥ ጆሮውም ከመስማት አልደነቈረችም፤*
*ነገር ግን **በደላችሁ** በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል።*

*ዘዳግም* 24:16 (*ሕዝቅኤል* 18:4---*ኃጢአት የምትሠራ ነብስ እርሷ ትሞታለች።*)

*አባቶች ስለ ልጆች አይገደሉ፥ ልጆችም ስለ አባቶች አይገደሉ፤ ነገር ግን ሁሉ **እያንዳንዱ በኃጢአቱ ይገደል።***

**ኢሳያስ 64:6**(በተጨማር መክብብ 7:20 ይመልከቱ)

***ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፥** ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው፤ ሁላችንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፥ በደላችንም እንደ ነፋስ ወስዶናል።*

ሆሴዕ 5:15

***በደላቸውንም እስኪያውቁ ድረስ፥** ፊቴንም እስኪሹ ድረስ ሄጄ ወደ ስፍራዬ እመለሳለሁ፤ በመከራቸው ጊዜ እጅግ አድርገው ፊቴን ይፈልጋሉ።*

***ዳንኤል* 12:2** (በተጨማሪ13:14 ኢሳያስ 26:19 እዮብ 19:26 *መዝሙር* 49:15)

በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኵሌቶቹ **ወደ ዘላለም ሕይወት**፥ እኵሌቶቹም ወደ እፍረትና **ወደ ዘላለም ጕስቍልና**።

**ዘኍልቁ 23:19** (በተጨማሪ 1ኛ ሳሙኤል 15:29**)**

**ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም** ።የተናገረውንስ አይፈጽመውምን? እርሱ ያለውን አያደርገውምን? ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም።

**ኤርምያስ 31:3** (ዘዳግም 7:6-10, 12-13)

እግዚአብሔርም ከሩቅ ተገለጠልኝ እንዲህም አለኝ። በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ፤ ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ።

ሰባዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻህፍት እየሱስ የእስራኤል መሢህ መሆኑን ያስረዳሉ።

በሁሉ ላይ ቅዱስ ስምህን ከፍ ከፍ አድርገሃልና።(መዝሙር 138፡2)

**አቤቱ፥ ቃልህ በሰማይ ለዘላለም ይኖራል።**

**(መዝሙር 119:89)**

**የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።**

**(ኢሳያስ 40: 8)**

**ንጉሱ የእየሱስ ከተናገራቸው ቃላት ጥቂቶቹ------**

**ዮሐንስ 5:39-40**

እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም።

**ዮሐንስ 8:21 ,24** ኢየሱስም ደግሞ እኔ እሄዳለሁ ትፈልጉኛላችሁም በኃጢአታችሁም ትሞታላችሁ እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም አላቸው።እንግዲህ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ አልኋችሁ፤ እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁና አላቸው።

**ሉቃስ 24:25-27**

እርሱም እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፤ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው። <u>ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው።</u>

**ሉቃስ 24 :44-47**

እርሱም። ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው። ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል።

**ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።**

**ዘፀዓት 20:3**

**አንተስ ብትሰማኝ ሌላ አምላክ አይሆንልህም፥ ለሌላ አምላክም አትሰግድም።መዝሙር 81:9**

**ዘዳግም 12:1-4**

በምድር ላይ በምትኖሩበት ዘመን ሁሉ የአባቶቻችሁ **አምላክ እግዚአብሔር** ለመውረስ በሰጣችሁ አገር፥ የምትጠብቁአትና የምታደርጉአት ሥርዓትና ፍርድ እነዚህ ናቸው።
እናንተ የምትወርሱአቸው አሕዛብ አማልክቶቻቸውን ያመለኩባቸውን በረጅም ተራሮች በኮረብቶችም ላይ ከለምለምም ዛፍ በታች ያለውን ስፍራ ሁሉ ፈጽማችሁ አጥፉአቸው፤
መሠዊያቸውንም አፍርሱ፥ ሐውልቶቻቸውንም ሰብብሩ፥ የማምለኪያ ዐፀዶቻቸውንም በእሳት አቃጥሉ፥
የአማልክቶቻቸውንም የተቀረጹ ምስሎች አንከታክቱ፤ ከዚያም ስፍራ ስማቸውን አጥፉ።
ለአምላካችሁ **ለእግዚአብሔር** እንዲህ ያለ ሥራ አትሥሩ። (በተጨማሪ ዘዳግም 7:4-6 25-26 **ይመልከቱ**)።
ዘዳግም 32:16-17
በሌሎች አማልክት አስቀኑት፥ በርኵሰታቸውም አስቈጡት። እግዚአብሔር ላልሆኑ አጋንንት፥ለማያውቋቸውም አማልክት፥ በቅርብ ጊዜ ለተነሡ ለአዲሶች አባቶቻቸውም ላልፈሩአቸው አማልክት ሠዉ።

**እየሱስ እንግዳ ዓምላክ አይደለም ።**

**የሕያው አምላክ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ የእስራኤል ቅዱስ ነው።**

ዮሐንስ 10:30-38 እኔና አብ አንድ ነን።አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ። ኢየሱስ ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው። አይሁድም ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት። ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው። እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው፥ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ እናንተ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለም ም የላከውን። ትሳደባለህ ትሉታላችሁን? እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ አትመኑኝ፤ ባደርገው ግን እኔን ስንኳ ባታምኑ **አብ በእኔ እንደ ሆነ እኔም በአብ እንደ ሆንሁ** ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ <u>ሥራውን እመኑ።</u>

“የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፤ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፥ ለተማረኩትም ነጻነትን ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል። **የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመት** አምላካችንም የሚበቀልበትን ቀን እናገር ዘንድ፥ የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ”።(ይህን ቃል **የኢዮቤልዩ አመት** ተናገረ በዚሁ በኢዮቤልዩ አመት ይመለሳል) ።

“ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም።” ዮሐንስ 5:22-23

**<u>የእየሱስ መለኮታዊነት በቅዱስ ብሉይ መፃህፍት እንደተገለጸው</u>**

የእግዚአብሔርና (ኤሎሂም) የንጉሱ እየሱስ ግንኙነት በብሉይ መፃህፍት ለናሙናነት የተጠቀሱ 24 (ሃያ አራት) ጥቅሶች ።

ኢሳያስ 9:6-7 ሕፃን ተወልዶልናልና፥ **ወንድ ልጅም** -----**ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት** ተብሎ ይጠራል።ኢሳያስ59:15-20 -------ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት፥ ጽድቁም አገዘው ።

ኢሳያስ 59:17 -----ጽድቅንም እንደ ጥሩር ለበሰ፥ በራሱም ላይ የማዳንን ራስ ቍር አደረገ፥

ኢሳያስ 52:10 13-15 እግዚአብሔር የተቀደሰውን ክንዱን-------

ኢሳያስ53:1-12 የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጦአል?--**ጻድቅ ባሪያዬም**--የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ-**በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።**

ኢሳያስ 40:9-11 ጌታ እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይመጣል ክንዱም ስለ እርሱ ይገዛል

ኢሳያስ 25:6-10 የእግዚአብሔርም እጅ በዚህ ተራራ ላይ ታርፋለች፥

ኤርምያስ 23:5-6 ለዳዊት ጻድቅ ቍጥቋጥ የማስነሣበት ዘመን ይመጣል

ኤርምያስ 33:14-24 ለዳዊት የጽድቅን ቍጥቋጥ አበቅልለታለሁ

ኢያሱ 5:14 እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ(እየሱስ) ሆኜ አሁን መጥቼአለሁ

ዘካርያስ 9:14 ጌታ እግዚአብሔርም (እየሱስ) መለከትን ይነፋል

መዝሙር 24:7-10 የክብርም ንጉሥ(እየሱስ)

መዝሙር 110:1 እግዚአብሔር ጌታዬን ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው።

ዳንኤል7:9-14(ኢሳያስ42:8 48:11) <u>ክብሬን</u> ለሌላአልሰጥም።እነሆ፥ **የቀድሞው ነገር ተፈጸመ፥** አዲስ ነገርንም እናገራለሁ

ዘፍጥረት 1:26 3:22 11:7ኢሳያስ 6:8[ሰውን **እንደ**---]

ኢሳያስ 42:1-8 እነሆ ደግፌ የያዝሁት ባሪያዬ እርሱም ለአሕዛብ ፍርድን ያወጣል።

ኢሳያስ 48:16 አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል።

ኢሳያስ 49:1-8(7) ሰዎች ለሚንቁት ሕዝብም ለሚጠላው ለገዥዎች ባሪያ --ስለ ታማኙ ስለ እግዚአብሔር ስለ መረጠህም ስለ እስራኤል ቅዱስ

ኢሳያስ 63:5 የገዛ ክንዴ (እየሱስ)መድኃኒት (እየሱስ)አመጣልኝ፥

ኢሳያስ 66:14 **የእግዚአብሔርም እጅ** ለሚፈሩት ትታወቃለች

ምሳሌ30:4 ስሙ ማን የልጁስ ስም ማን ነው?

ዘኍልቁ24:17 ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል፥ከእስራኤል በትር ይነሣል፥

ዘዳግም 18:18-19 እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ----ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፥ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ።

መዝሙር 82:6 አማልክት ናችሁ፥ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ፤

መዝሙር 8:4 ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው

ሆሴዕ 2:21 ለዘላለምም ለእኔ እንድትሆኚ አጭሻለሁ፤ በጽድቅና በፍርድ በምሕረትና በርኅራኄ አጭሻለሁ። ይህን ዕውነት የሚያረጋግጡ ጥቂት **<u>የአዲስ ኪዳን</u>** ጥቅሶች-----እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ ሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ። እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ --

[ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል፤-------]
















12/15/13